# ኖቭል ኮሮናቫይረስ በሽታ
# COVID-19

## COVID-19 ምንድን ነው?

COVID-19 “ኖቭል” ኮሮና ቫይረስ በተባለ አዲስ ቫይረስ የሚከሰት የመተንፈሻ አካል በሽታ ነው። ኮሮና ቫይረስ እንደ ጉንፋን ያሉ የመተንፈሻ አካል በሽታዎችን ያስከትላል።



## የሚሰራጨው እንዴት ነው?

COVID-19 የሚሰራጨው ከማስነጠስ ወይም ከሳል በሚመነጩ የፈሳሽ ጠብታዎች አማካይነት ነው። የእጅ መጨባበጥና ምግብ ወይም መጠጥ መጋራትን ጨምሮ ከሌሎች ጋር በሚደረግ የቅርብ ንክኪ አማካይነትም ይሰራጫል።

## ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?

የ COVID-19 ዋና ዋና ምልክቶች ትኩሳት፣ ሳል እና የትንፋሽ ማጠር ናቸው። አንዳንድ ሰዎችም የሰውነት ሕመምና የጉሮሮ ቁስለት ይኖራቸዋል።













## የበለጠ ስጋት ያለበት ማነው?

አረጋውያን፣ ነባር የጤና ችግሮች ያለባቸው በማናቸውም ዕድሜ ክልል ላይ ያሉ ሰዎችና ነፍሰ ጡር ሴቶች በ COVID-19 ምክንያት ለሚከሰት ከባድ ሕመም የመጋለጥ ስጋታቸው የጨመረ ነው።

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ civil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

# ራስዎንና ማህበረሰብዎን ይጠብቁ።

## በተቻለ መጠን ቤት ውስጥ ይቆዩ። በተለይም ሕመም ካለብዎት።




## ወደ ስራ ወይም ወደ ግሮሰሪ መደብር ይሄዳሉ?



ከሌሎች ሰዎች የ6 ጫማ ርቀት ላይ ይቆዩ።



የፊት ማስክ ያድርጉ።



እጆችዎን ይታጠቡ።




የእጅ ማጽጃ ፈሳሽን ይጠቀሙ።



ሲያስልዎና ሲያስነጥሱ አፍዎን ይሸፍኑ።



በቤትዎ ውስጥ ያሉ አካላትን ያጽዱ።



ወደ ዶክተር ከመሄድዎ በፊት ስልክ ይደውሉ።



አፍዎን፣ አፍንጫዎን ወይም ዓይንዎን አይነካኩ።

## የ COVID-19 አጣዳፊ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ከታዩብዎ ወደ **9-1-1** ይደውሉ

- ለመተንፈስ መቸገር
- በደረት አካባቢ የማያቋርጥ ሕመም ወይም ጫና
- በድንገት መደናገር
- ለሌሎች ምላሽ ለመስጠት አለመቻል
- የከንፈር ወይም የፊት ገጽታ ሰማያዊ ሲሆን

የአስተርጓሚ አገልግሎት ለማግኘት **DOH.WA.GOV/Coronavirus** ወይም **Coronavirus.wa.gov** የሚለውን ይጎብኙ፣ ወደ **1-800-525-0127** ደውለው # ይጫኑ ወይም ለተጨማሪ መረጃ **"Coronavirus"** ብለው ወደ **211211** ይላኩ።